ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

**የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የ2016 ዓ.ም አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ።**

ለተማሪዎች፣ወላጆች፣መምህራን፣ የትምህርት ማህበረሰብ ፣ አጋር ድርጅቶች እንዲሁም ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እንኳን ለ2016 ዓ.ም በሰላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ያለፈው የ2015 ዓ.ም በትምህርት ሴክተሩ ያሉ ስብራቶችን ለማስተካከልና ትምህርትን በፍትሃዊነት ለዜጎች ለማድረስ በርካታ የለውጥ አጀንዳዎችን አቅደን የተገበርንበትና መሰረት የጣልንበት ዓመት ነበር።

በተለይም በትምህርት ስርዓቱ አዲስ የትምህርት ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ ከማድረግ ጀምሮ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚረዱ ወሳኝ ተግባራትን ፈጽመናል ።

እነዚህን ለውጦች በትምህርት ሴክተሩ እንዲመዘገቡ የሰሩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ሰራተኞ፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ በየደረጃው ያሉ የትምህርት አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ አጋር ድርጅቶችና ቁለፍ ባለድርሻ አካላቶችን በሙሉ ላመሰግን እወዳለሁ።

በሃገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች ከመሆናቸው የተነሳ ለመማር ማስተማር ስራው ምቹ ባለመሆናቸው ይህንን በመንግስት አቅም ብቻ ለመቅረፍ ስለማይቻል “ትምህርት ለትውልድ” የትምህርት ቤቶች መሰረተ ልማት ማሻሻል ሀገራዊ ንቅናቄ በሀገር አቀፍ ደረጃ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በተገኙበት በማስጀመር በሁሉም ክልሎች እስከ ወረዳ ድረስ በማውረድ ከፍተኛ የህዝብ ንቅናቄ የተጀመረበት ዓመት ነበር።

ምንም እንኳን በአንደኛ ደረጃ ትግበራ ወቅት የመጽሐፍት እጥረት ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖብን የነበረ ቢሆንም በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት አዲሱ ስርዓተ ትምህርት በመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ሙሉ ትግበራ ውስጥ የተገባበት እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሙከራ ትግበራ የተደረገበት ዓመት ነበር።

እንደ ሃገር ከፍተኛ የሞራል ውድቀትና ስብራት ገጥሞን የነበረውን የትምህርት ምዘናና ፈተና አስተዳደር ስርዓትን ለማስተካከል ለሁለተኛ ጊዜ በዚህ ዓመት ከ840, 859 በላይ ተማሪዎችን ከስርቆትና ኩረጃ ነጻ በሆነ መልኩ በዩኒቨርሲቲዎች በስኬታማነት መፈተን የተቻለበትም ዓመት ነበር።

ግብዓታቸው የተሟላላቸው ከሁሉም ክልሎች በትምህርታቸው የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ተመርጠው የሚገቡባቸው ልዩ አዳሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመላ ሀገሪቱ ለመገንባት በተለያዩ ክልሎች የቅድመ ግንባታ ሥራ የተጠናቀቀበት ዓመት ነበር።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ትምህርታቸውን አቋርጠው የነበሩ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የመመለስና መልሶ ግንባታ እየተሰራ ሲሆን አዲስ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤት የሚል የትምህርት ቤቶች ዲዛይን ተሰርቶ በዲዛይኑ መሰረት 50 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ግንባታ ስራ የተጀመረበት ዓመትም ነበር።

ከከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አንጻር ከተቋማቱ የሚወጡ ምሩቃን ብቃታቸው የተረጋገጠና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተናን በተሳካ መልኩ በሁሉም የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች መስጠት የተችሏል።

የትምህርት ሰርተፊኬቶችን ትክክለኛነት ለመለየት በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች የሚሰሩ ሰዎችን የትምህርት ሰርተፊኬት የማጥራት ስራ የተጀመረበት ዓመት ነበር።

ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት እንዲረጋገጥ፣ ከፖለቲካዊም ሆነ አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው የመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራዎችን በላቀ መልኩ መፈጸም እንዲያስችላቸው ዩኒቨርስቲዎች ራስ ገዝ እንዲሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ያቀረበው ሰነድ በአዋጅ 1294/2015 የጸደቀበት እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያው ራስ ገዝ ዩኒቨርስቲ እንዲሆን የተወሰነበት፣ይህንንም ሽግግር በብቃት ለማስፈጸም ለዩኒቨርሲቲው አዲስ አስተዳደር የተሰየመበት ዓመት ነበር።

በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ፕሮግራሞች አከፋፈት ዩኒቨርሲቲዎቹ ባላቸው ከባቢያዊ ጸጋ መሰረት እንዲሆን ዩኒቨርሲቲዎችን በተልዕኮና ትኩረት መስካቸው የማደራጀት ስራም በዚሁ ዓመት ተጠናቋል።

በከፍተኛ ትምህርት የፕሮግራሞች መዋቅር፣ሥርዓተ ትምህርትና በፕሮግራሞች የእርዝማኔ ለውጥ የተደረገበት በዚህም የጋራ ኮርሶች ልየታ፣ የመርሃ ስርዓተ ትምህርት እና የሞጁል ዝግጅት ስራዎች ተፈጽመዋል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው በትግራይ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችን መልሶ ለማቋቋም ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ዩኒቨርሲቲዎቹ ወደ መማር ማስተማር ስራ እንዲመለሱ የተደረገበት እና በርካታ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የለውጥ አጀንዳዎች የተተገበሩበት ዓመት ነበር።

**ውድ ኢትዮጵያውያን ፡-**

እንደሚታወቀው ትምህርት ትውልድ የማስቀጠል ጉዳይ ነው በመሆኑም ባለፈው አመት የጀመርናቸውን የለውጥ ስራዎች በመጪው 2016 ዓ.ም አዲስ አመትም አጠናክረን በልዩ ትኩረት የምንሰራ ይሆናል።

በተለይም ስርዓተ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ፣የመጽሃፍት ህትመትና ስርጭት በአጭር ጊዜ ተማሪዎች እጅ ላይ እንዲደርስ ማድረግ፣ የትምህርት ቤቶችን መሰረት ልማት ማሻሻል፣የፈተና ስርዓቱ ከኩረጃና ሰርቆት ነጻ እንዲሆን የጀመርነውን ስራ አጠናክረን መቀጠልና ኢንተርኔት ባላቸው አካባቢዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ድብልቅ (Hybrid) የፈተና አሰጣጥ የምንጀምርበት ዓመት ይሆናል።

የከፍተኛ ትምህርት ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች መግቢያ ፈተና፣ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ እንዲሆኑ መደገፍ፣ የመሳሰሉትን ትኩረት ሰጥተን የምንሰራበት ዓመትም ይሆናል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፡-**

ትምህርት ላይ የምንሰራው ስራ ለትውልድ ነውና የጀመርናቸው የትምህርት ሪፎርሞች እንዲሳኩ በተለይም የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል የጀመርነውን ትምህርት ለትውልድ ህዝባዊ ንቅናቄ የያዝነው ራዕይ እንዲሳካ ሁላችሁም ገንዘቡ እውቀቱና ጉለበቱ ያላችሁ ወላጆች፣ ባለሃብቶች ፣ ታወቂ ግለሰቦች፣ አጋር ድርጅቶች እንዲሁም በውጪ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አቅማችሁ የቻለውን ሁሉ ድጋፍ እንድታደርጉ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

በመጨረሻም በአዲሱ አመት ወደ አጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምትገቡ ተማሪዎች፣ መምህራንና የትምህርት አመራሮች መልካም የትምህርት እና የሥራ ዘመን እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።

መልካም አዲስ አመት !

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር